የፌዴራል የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን

የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

እንደገና ለማሻሻል የወጣ

አዋጅ ቁጥር------/2013

---------/2013 ዓ/ም

አዲስ አበባ

እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር------/2013

የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሀገራችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚገታ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የህግ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በሀገራችን የተጀመረውን የልማት፣ የሰላም እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ለማፈጠንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

በመልካም ስነ-ምግባር የተገነባ፣ ሙስናን የሚፀየፍ እና በፅናት የሚታገል ህብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኮሚሽኑ አሠራር የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ ኮሚሽኑ ተቋማዊ እና የአሰራር ነፃነት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣

በሙስና መከላከል ላይ የተፈጠረውን ክፍተት ለማስተካከል እና ለኮሚሽኑ በተለያዩ አዋጆች ተሰጥተውት የነበሩትን የተበታተኑ ስልጣንና ተግባራት በአንድ ላይ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ኮሚሽኑ በሀገር ደረጃ የፀረ ሙስና ትግሉን የመምራት እና የማስተባበር ሚናውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን የኃላፊነት ወሰኑን በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የሙስና መከላከል ተግባር በአንድ ተቋም ተጀምሮ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ኮሚሽኑ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት የህግ ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ ከፀረ ሙስና ትግል አኳያ በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ ሀገሪቱን በብቃት እንዲወክል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለኮሚሽኑ ተሰጥተውት ከነበሩ ስልጣን እና ተግባራት ውስጥ የተወሰኑት ግልፅነት የሚጎላቸው ስለሆነ የበለጠ ግልፅት መፍጠር በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህግ መንግስት አንቀፅ 55(1) መሰረት የሚከተለው አዋጅ ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር----/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ኮሚሽን’’ ማለት የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፣
2. “ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር’’ ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ነው፣
3. “የመንግስት መስሪያ ቤት’’ ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግስቱ ሰራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፣
4. “የመንግስት የልማት ድርጅት’’ ማለት የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፣
5. “ህዝባዊ ድርጅት’’ ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳደር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን የሚከተሉትን አያካትትም፡-

    ሀ. የሃይማኖት ድርጅትን፣

    ለ. የፖለቲካ ድርጅትን(ፓርቲን)፣

    ሐ. የዓለም አቀፍ ድርጅትን፣ እና

    መ. ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን።

6. “የመንግስት ባለስልጣን’’ ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፣ የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ሚኒስቴሮች፣ ሚኒስቴር ዴኤታዎች፣ ኮሚሽነሮች፣ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ ዳይሬክተሮች፣ ምክትል ዳይሬክተሮች፣ ባለስልጣኖች፣ ምክትል ባለስልጣኖች፣ ስራአስኪያጆች፣ ምክትል ስራ አስኪያጆች፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንትና ዳኞች፣ ዋና ጠቅላይ አቃቢ ህግ፣ ምክትል ጠቅላይ አቃቢ ህግ እና አቃቢያን ህጎች፣ የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ የኮሌጅ ዲኖችንና ምክትል ዲኖች፣ የሆስፒታል ስራ አኪያጆችና ምክትል ስራአስኪያጆች፣ ሌሎች በተመሳሳይ በሁሉም ደረጃ የሚገኙትን የስራ ኃፊዎች ያካትታል፣
7. “የመንግስት ሰራተኛ’’ ማለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ በማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በቋሚነት ወይም በጊዜዊነት ከ 3 ወር በላይ ለተራዘመ ጊዜ የሚሰራ ሰው ነው፣
8. “የመንግስት የልማት ድርጅት ባለስልጣን” ማለት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የድርጅቱ የዳይሬክተሮችና የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላትን፣ የድርጅቱ ኃላፊ እና ምክትል ኃላፊዎችን፣ በቦርዱ ወይም በስራ አመራሩ ወይም በሌላ ስልጣን በአለው አካል የተሾመ ወይም የተመደበ የስራ ኃላፊን ያካትታል፣
9. “የህዝባዊ ድርጅት ባለስልጣን” ማለት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የድርጅቱ የዳይሬክተሮችና የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላትን፣ የድርጅቱ ኃላፊ እና ምክትል ኃላፊዎችን፣ በቦርዱ ወይም በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በሌላ ስልጣን በአለው አካል የተሾመ ወይም የተመደበ የስራ ኃላፊን ያካትታል፣
10. “የመንግስት የልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ” ማለት በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በቋሚነት ወይም በጊዜዊነት ከ 3 ወር በላይ ለተራዘመ ጊዜ የሚሰራ ሰው ነው፣

11. “የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች” ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ስራውን በየተቋማቱ ለማስራት የሚያደራጇቸው አደረጃጀቶች ናቸው፣

12. “የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ” ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ተመድቦ ወይም ተቀጥሮ የሚሰራ ማለት ነው፣

13. “አደረጃጀቶች” ማለት ኮሚሽኑ በመንግስት ወይም በግል የትምህርት ተቋማት ወይም የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ውስጥ መልካም ስነምግባርን ለመገንባት እና ሙስናን ለመከላከል እንዲያስችለው የሚያደራጇቸው የተማሪዎች ስነምግባርና የፀረ ሙስና ክበባት እና ሌሎች ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ናቸው፣

14. “ለህዝባዊ አገልግሎት የተሰበሰበ ሃብት” ማለት የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን ወይም ህብረተሰቡን በአጠቃላይ ለመርዳት ወይም ለመደገፍ ወይም ለማበረታተት ወይም ለማልማት ታስቦ የተሰበሰበ ወይም ለዚሁ ዓላማ እንዲውል በማንኛውም መንገድ የተገኘ እና በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ይህን ዓላማ ለማሳካት ተብሎ በተደራጀ ወይም በተቋቋመ ኮሚቴ የሚተዳደር ወይም የሚንቀሳቀስ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሃብት ነው፣

15. “የባንክ ሂሳብ” ማለት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ፣ ወርቅ እና የመሳሰሉት ውድ እቃዎች እንዲሁም አንድ ደንበኛ ከባንኩ ጋር የሚያደርጋቸውን ማናቸውንም ግንኙነቶች /ትራንዛክሽኖች/ የሚያጠቃልል ነው፣

16. “ጠቋሚ” ማለት ሊፈፀም ነው ብሎ ያመነውን የሙስና ወንጀል ወይም የሃብት ምዝገባ ትክክለኛ አለመሆንን የሚመለከት መረጃ ለኮሚሽኑ ወይም ለስነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፣

17. “ሀገራዊ የፀረ ሙስና ፖሊስ እና ስትራቴጂ” ማለት መልካም ስነምግባርን በመገንባት፣ ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ረገድ በአጭር እና በረጅም ጊዜ ሀገሪቱ ልትደርስበት የምታስበውን ደረጃ የሚያመላክት ሀገራዊ ሰነድ ነው፣

18. “ሰው’’ ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. የዖታ አገላለፅ

ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

ክፍል ሁለት

ስለኮሚሽኑ መቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር

4. የኮሚሽኑ መቋቋም

1. የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ከዚህ በኋላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በአዋጅ ተቋቁሟል፣
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፣
3. የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የራሳቸውን ኮሚሽን ያቋቁማሉ።

5. ስለ ኮሚሽኑ የአሰራር ነፃነት

ኮሚሽኑ ሙስና ለመከላከል በሚያደረገው እንቅስቃሴ ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት እና አመራር ነፃ ነው።

6. ዋና መስሪያ ቤት

1. የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፣

7. የኮሚሽኑ ዓላማዎች

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የትውልድ ስነምግባር እና የሞራል ግንባታ እሴቶችን በብቃት መገንባት፣
2. የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል፣
3. ለፀረ ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆነ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህዝቡ የፀረ ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማደረግ፣
4. በህግ የተሰጡትን ተግባር እና ኃላፊነት ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፣
5. በመንግስት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ሃብት እና የገቢ ምንጮቻቸውን በማሳወቅ፣ በመመዘገብ፣ በተደራሽ ማድረግ፣ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ የግልፅነት እና የተጠያቂነትን ስርዓት መፍጠር ነው።

8. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ሀገራዊ የፀረ ሙስና ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያስፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
2. በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚሾሙ ወይም የሚመደቡ ወይም የሚቀጠሩ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የስነምግባር እና የሙስና መከላከል ስልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል፣
3. በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የተሰጡ የመፍትሄ /የማሻሻያ/ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ይወስዳል፣

4. ኮሚሽኑ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጠር ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም አስፈላጊውን ማስተካከያ የማድረግ ስልጣን አለው። ሆኖም ግን በተደረገው ክትትል ሙስና ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ ሲኖረው አግባብነት ላለው ምርመራ አካል ያቀርባል፣

5. የህዝብ ተመራጮችን፣ የመንግስት ተሿሚዎችን እና የመንግስት ሰራተኞችን፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ መረጃው በአግባቡ ተደራጅቶ እንዲያዝና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣

6. ለሃብት ምዝገባ፣ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሶፍት ዌየር ያለበለፅጋል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣ ያስተላልፋል፣ ያስተዳድራል:: የፍትህ አካላት መረጃ ሲጠይቁ ይህንኑ ከዳታ ቤዝ የተገኘውን መረጃ ይሰጣል፣

7. የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ከመቆጣጠር እና ከመወሰን ስልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጥቅም ግጭትን ይከላከላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

8. ሙስናን በመታገል እና በመከላከል ረገድ ጥሩ ውጤት ያስገኙ መስሪያ ቤቶችን፣ ድርጅቶችን ግለሰቦችን፣ እና ከበባትን አወዳድሮ እውቅና የሚያገኙበትን እና ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርዓትና መለኪያ ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

9. ለህዝብ ተመራጮች፣ ለመንግስት ተሿሚዎች፣ ለመንግስት ሰራተኞች፣ ለመንግስትና ለህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃፊዎች እና ሰራተኞች የሚያገለግል የስነምግባር ደንብ ያዘጋጃል፣ ያስፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

10. በመንግስት መስሪያቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭነትን ጥናት ያካሂዳል። እንደአስፈላጊነቱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣

11. የስነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች እና በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ያደራጃል፣

12. የፀረ ሙስና ህጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ስለአፈፃፀማቸው የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

13. በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የስነምግባር መከታታያ ዳይሬክቶሬቶችን ወይም ቡድኖችን ወይም ባለሙያዎችን ያደራጃል፣ ይመድባል፣ ያሰማራል፣

14. የክልል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖችን ያተባብራል፣ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ያድረጋል፣

15. ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አካላት ጋር ሀገሪቱን በመወከል ግንኙነት እና ትብብር ያደርጋል፣

16. በሀገሪቱ ህግ እና ፖሊሲ መሰረት አለም አቀፍ እና አህጉራዊ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽኖችን እና ትብብሮች ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

17. አለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽኖን አፋፃፀም በተመለከተ ሀገሪቱን ይወክላል፣

18. የስነምግባር ትምህርትን ለማስፋፋት እና መልካም ስነምግባርን ለመገንባት እንዲያስችለው የራሱ ሚዲያ እንዲቋቋም ይደረጋል፣

19. በስነምግባር ግንባታ እንዲሁም በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ስልጣን የተሰጣቸውን መስሪያ ቤቶች የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ይቀበላል፣

20. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል እና ይከሰሳል፣

21. በህግ የሚሰጡትን እና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

9. የኮሚሽኑ አቋም

1. ኮሚሽኑ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚኒስቴር ማዕረግ የሚሾም ኮሚሽነርና በሚኒስቴር ዴኤታ ማዕረግ የሚሾሙ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ እና

2. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል።

10. የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፣

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ. የኮሚሽኑን መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅሞቻቸውን በማዘጋጀት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ በማፀደቅ ክፍያ ይፈፅማል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በተመለከተ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፣

ሐ. በዚህ ህግ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎችን ጠብቆ ደንብ አዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይሾማል፣ ይመድባል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳደራል፣ ያሰናብታል። ዝርዝሩ አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፣

ሠ. የኮሚሽኑን አመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ረ. ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀት እና በአዘጋጀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሰ. ኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፣

ሸ. የኮሚሽኑን ጠቅላላ የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ቀ. በሃብት ምዝገባ፣ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭትን በማስተዳደር ሂደት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የባንክ ሂሳብ እንዲፈተሽ እና አስፈላጊው መረጃ እንዲሰበሰብ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፣

3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11. የምክትል ኮሚሽነሩ ስልጣን እና ተግባር

1. ምክትል ኮሚሽነሩ፡-

ሀ. የኮሚሽኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፣

ለ. በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፣

ሐ. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፣

መ. ከኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

2. ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል፣

3. ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ በኮሚሽነሩ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል።

12. የኮሚሽነሩ እና የምክትል ኮሚሽነሩ የስራ ዘመንና ከስራ ስለመነሳት

1. የኮሚሽነሩ እና የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመን ለስድስት አመት ይሆናል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን እንደገና ሊሾም ይችላል፣

2. ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የተሾመበት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከሥራው አይነሳም፣

ሀ. አግባብነት ባለው የሥነ ምግባር ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

ለ. ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና የቅልጥፍና ጉድለት ላሳይቷል ተብሎ ሲታመን፣

ሐ. በጤና ችግር ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

መ. የጡረታ እድሜ ላይ ሲደረስ፣

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 2 (ከሀ-ሐ) ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በሚቋቋም ኮሚቴ ተጣርቶ ሲረጋገጥ እና ለምክር ቤቱ ቀርቦ በ 2/3 ኛ ድምፅ የምክር ቤቱን ውሳኔ ሲያገኝ ይሆናል።

13. ስለኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥር ሁኔታ

የኮሚሽኑ ሠራተኞች የቅጥር፣ አስተዳደርና ስንብት ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል።

14. ቃለመሀላ ስለመፈፀም

በኮሚሽኑ የተቀጠረ ማንኛውም ሠራተኛ ለፌደራሉ ህገ መንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ህዝባዊ አደራና ሙያዊ ሀላፊነት ለመወጣት ቃለመሀላ ይፈጽማል። የቃለመሀላው ዝርዝር ይዘት በደንቡ ይወሰናል።

15. የኮሚሽኑ ሠራተኞች መብት

1. ማንኛውም የኮሚሽኑ ሠራተኛ የተወካዮች ምክር ቤት በሚያፀድቀው ልዩ የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ክፍያ መሰረት ደመወዝ ይከፈለዋል፣
2. የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ፡-
   ሀ. በሠራተኛው ስምምነት፣
   ለ. በፍርድ ቤት ትእዛዝ፣
   ሐ. በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ ወይም/ሐ/ መሠረት ከሠራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሶስተኛ አይበልጥም፣
4. ማንኛውም የኮሚሽኑ ቋሚ ሠራተኛ በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፣

5. የኮሚሽኑ ሠራተኛ፡-
   ሀ. ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በኮሚሽኑ ወጪ ድጋፍና የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል። ዝርዝር አፈፀፃሙ በደንብ ይወሰናል፣
   ለ. በማንኛውም አጋጣሚ የበላይ ሀላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፣ ስህተት ሲያይ የመጠቆም፣ በውይይት ችግሮችን የመፍታት እንዲሁም የስልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣
   ሐ. በደንቡ በሚወሰነው መሠረት ይግባኝ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፣
   መ. ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደርስበት ጉዳት ዘላቂ ወይም ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን ያጣ የኮሚሽኑ ሠራተኛ አግባብ ባለው ህግ መሰረት የጉዳት ካሳ ይከፈለዋል፣ በጡረታ ህግ መሰረት የተሰጠው መብት ይከበርለታል። ዝርዝር አፈፀጻሙ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፣
   ሠ. የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከስራቸው ልዩ ባህሪ ጋር በተያየዘ ደመወዝ እና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን አስጠንቶ በማቅረብ እና በተወካዮች ምክር ቤት በማፀደቅ ተግባራዊ ይደረጋል፣
   ረ. በትርፍ ጊዜው ከሥራው ጋር የጥቅም ግጭት በማይፈጥር ሥራ ላይ ለመሰራት መሥሪያ ቤቱን በማሳወቅ ለመስራት ይችላል። ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

16. ከግብር ነፃ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 15 በንዑስ አንቀፅ 5/መ/ መሠረት የሚከፈል የጉዳት ካሳ ከፍያ ከግብር ነፃ ይሆናል። እንዲሁም በእዳ ሊከበር ወይም በማቻቻያነት ሊቀነስ ወይም ባለመብቱ ሊያስተላልፈው አይችልም።

17. ሰራተኛን ከሥራ አግዶ ስለማቆየት

1. የኮሚሽኑ ሠራተኛ ከሥራ ታግዶ መቆየት ለሥራው አፈፃፀም ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ሠራተኛውን ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ከሥራና ደመወዝ አግዶ ለማቆየት ይቻላል፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም የኮሚሽኑ ሠራተኛ በወንጀል ወይም በዲሲፕሊን ጥፋት በህግ የተከሰሰ እንደሆነ እና ተመስክሮ ጥፋቱ ከሥራው የሚያስወጣው መሆኑ ሲገመት ለተጨማሪ አንድ ወር ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ይችላል። ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል።

18. ስለይርጋ ጊዜ

1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የምርመራውን ጊዜ ሳይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣
2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሳይወሰድ የቀረው ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል።

19. በጀት

ኮሚሽኑ ለስራ የሚያስፈልገውን በጀት በማዘጋጀት ለተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል።

20. የሂሣብ መዛግብት

1. ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራሉ ዋና ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራል።

ክፍል ሶስት

የስነምግባርና መከታታያ ክፍሎችን ስለማደራጀት እና ኮሚሽኑ ከክልል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

21. የስነምግባር መከታታያ የስራ ክፍል ስለማደራጀት

1. ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ ምግባር ተግባራትን እና የሙስና መከላከል ስራን የሚያስተባብር እና የሚፈፅም የሥነ ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል ያደራጃል፣
2. ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነ ምግባር ተግባራትን እና የሙስና መከላከል ስራን የሚያስተባብር እና የሚፈፅም የሥነ ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል እንዲደራጅ ያደረጋል፣
3. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ይሆናል፣

4. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የመመደብ፣ የመቅጠር፣ የማዘወር እና የማሰናበት ተግባር የኮሚሽኑ ይሆናል። የሚደራጁት የስነምግባር መከታታያ ክፍሎች በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና በመንግስት ልማት ድርጅቶች በሚገኙ ዓላማ ፈጻሚዎች የስራ ደረጃ ጋር ትይዩ ይሆናል፣
5. ኮሚሽኑ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ፣ እንዲቀጠር፣ እንዲዛወር እና እንዲሰናበት ያደርጋል። የሚደራጁት የስነምግባር መከታታያ ክፍሎች በህዝባዊ ድርጅቶች በሚገኙ ዓላማ ፈጻሚዎች የስራ ደረጃ ጋር ትያዩ ያሆናል፣
6. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚደራጁት የሥነምግባር መከታታያ ክፍሎች ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖራቸውን የሥራ ግንኙነት፣ አደረጃጀት እና አሰራር ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው መመሪያ ይወሰናል፣
7. የሥነምግባር መከታታያ ክፍሎች ከሚደራጁበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅቶች ጋር የሚኖራቸውን የሥራ ግንኙነት ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው መመሪያ ይወሰናል።

22. ኮሚሽኑ ከክልል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት

1. ኮሚሽኑ በሀገር ደረጃ የስነምግባር እና የፀረ ሙስና ተግባራትን የመምራት እና የማስተባበር ተግባራትን የሚያከናውን ስለሆነ የክልል እና የከተማ አስተዳደሮች የሥነምግባር የፀረ ሙስና ኮሚሽኖችን ያስተባብራል፣ አስተዳደራዊ እና የቴክኒክ ድጋፍ ያድረጋል፣
2. ኮሚሽኑ ከክልል እና ከከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር የእቅድ፣ የሪፖርት እና የግንኙነት ስርዓት ይፈጥራል፣
3. የክልል እና የከተማ አስተዳደር የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች በየአካባቢያቸው ስላላው የፀረ ሙስና እንቅስቃሴ የሚመለከቱ ሪፖርቶችን እና ስታስቲካዊ መረጃዎችን በየጊዜው ለፌዴራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ይሰጣሉ።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

23. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

24. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

1. የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/2005 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 883/2007 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ህጐች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

25. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ---/2013 ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት